የሰ/መ/ቁ. 49958

የካቲት 12 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ግዮን ትራብልና ቱርስ ኃ/የተ/የግ/ማ - ነ/ፈጅ ዳንኤል ወርቅዬ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ዳንኤል አስፋው - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የሥራ ውል ማቋረጥን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ ያለአግባብ ከሥራ መሰናበቱን ጠቅሶ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ እንዲመለስ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ በአመልካች በኩል ሥር ፍ/ቤት የቀረበው ክርክር ተጠሪው የሥራ ሃላፊው ላይ አላስፈላጊ አምባጓሮ፣ ፀብ፣ ዛቻ፣ ስድብ በመፍጠሩ ተሰናብቷል የሚል ነው ጉዳዩን በመ/ደረጃ የተመለከተው የፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ሥራ አስኪያጅ ላይ እንደዛተ እንጂ አምባጓሮ ወይም ፀብ ስለፍጠሩ አልተረጋገጠም በሚል ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ሲል ፈርዷል፡፡ አመልካች የአምስት ወር ደመወዝ ለተጠሪ ከፍሎ ወደ ሥራ እንዲመለስ ሲልም ወስኗል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው የአመልካች ነ/ፈጅ ጥቅምት 21/2002 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው አቤቱታ ይዘት ተጠሪው የነዳጅ ያቀረበው ደረሰኝ የተጋነነ እና ታማኒነት የጐደለው በመሆኑ በሥራ አስኪያጁ ሲጠየቅ በአግባቡ ማስረዳት ሲገባው ጠብ አጫሪነት በመፍጠር ወይ አንተ ወይ እኔ እንኖራለን በማለት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ ረ መሰረት ጥፋት ስለመፈፀሙ መረጋገጡን

ስንብቱ ሕጋዊ ስለመሆኑ በአማራጭ ተጠሪው በአዋጁ አንቀጽ 43/1/ መሰረት ካሣ ተከፍሎት ሊሰናበት እንደሚገባ ራሱ የጠየቀው ዳኝነት የሥር ፍ/ቤቶች ማለፋቸው የሕግ ስሕተት መሆኑን ጠቅሶ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሻር አመልክቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ትሎትም በተጠሪ ተፈጽሟል የተባለው ድርጊት ከአዋጁ አንቀጽ 27/1/ረ አንፃር ለመመርመር የሚገባው ሆኖ ስላገኘው ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት አድርጓል ተጠሪ የካቲት 12 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ የሕግ ስሕተት የለውም ሲል እንዲጸና ጠይቋል፡፡

እኛም የቀረበውን አቤቱታ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት የተቻለው ተጠሪው የአመልካች ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ላይ የዛቻ ኃይለ ቃል እንደተናገረው ተመስክሯል፡፡ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው የተጠሪ ድርጊት የአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ረ የተደነገገውን ጥፋት ያሟላል የሚል ክርክር በአመልካች በኩል ቀርቧል፡፡ ይህንኑ ለመመረመር የተጠቃሹን ድንጋጌ ይዘት በዝርዝር መመልከት ይገባል፡፡ አንቀጽ 27/1/ረ እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

"እንደጥፋቱ ክብደት በሥራው ቦታ አምባጓሮ ወይም ጠብ አጫሪነት ተጠያቂ መሆን" ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ለማቋረጥ ከሚያስችሉ ምክንያቶች ሥር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የሥራ አስኪያጅን "ወይ አንተ ወይ እኔ እንኖራታለን" በማለት የዛተበት ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር መሆኑ ከመዝገቡ መረዳት ችለናል፡፡ ይህ የተጠሪው ድርጊት ከተጠቀሰው ድንጋጌ አንፃር ሲታይ የጠብ አጫሪነት ኃይለቃል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የተጠሪው የድርጊት ዛቻ ነው ካለ በኂላ ይህ ድርጊት ፀብ ድርጊት ሊባል እንደማይችል ጠቅሶ ይህ ክብደት ሊሰጠው አይገባም ብሏል፡፡ በኛ በኩል ስንመረመረው አንድ ሰራተኛ የአሰሪው ወይም የሥራ ኃላፊው ትእዛዝ ከሕግ ውጪ እስካልሆነ ድረስ ማክበር እና መፈጸም እንዳለበት ልብ ሊባል ይገባል፡፡ አንድ ሰራተኛ አሰሪው ወይም የሥራ ኃላፊው የሚሰጠውን ሕጋዊ ትእዛዛት መፈጸም እንዳለበት አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13/2/ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪ ስለሥራው አካሄድ በሥራ አስኪያጅ ሲጠየቅ አግባብ ባለው ሥርአት ማስረዳት ሲገባው ለምን ተጠየቅኩ በሚል ስሜት ኃይለ ቃል እና ዛቻ ማድረጉ የጠብ አጫሪነት ድርጊት መባል የሚገባው ስለመሆኑ ተረድተናል፡፡

ድርጊቱም የተፈፀመው በአመልካች ድርጅት የሥራ አስኪያጅ ላይ መሆኑ የተጠሪን ድርጊት ጥፋት ከባድነት አመልካች ነው፡፡ ስለሆነም የተጠሪው ድርጊት የአዋጁን አንቀጽ 27/1/ረ የተመለከተውን ጥፋት አያሟላም ሲል የሥር ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ሕግ ያስቀመጠውን የሰራተኛውን ግዴታ የሚመለከተውን ድንጋጌ እና የጥፋቱን አደገኛነት ከተጠቃሹ ድንጋጌ አንፃር በአግባቡ ሳያገናዝብ መሆኑን ስለተረዳን የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 40658 የሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 83563 የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ረ መሰረት በመሆኑ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ሊባል አይገባም ብለናል፡፡

ግራ ቀኝ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ